## ከ HIV ጋር በደንብ መኖር ይችላሉ

የ SAYFSM አገልግሎቶች መመሪያዎችን እና ተስፋን እንዲያገኙ ይረዱዎታል ፡፡

እነዚህ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች በ SAYFSM ለእርስዎ ተደራሽ ይሆናሉ፡

- በ HIV ለተያዙ አፍሪካውያን የስሜታዊ እና መንፈሳዊ ድጋፍ ቡድን
- የ HIV ምክር እና ምርመራ
- HIV/AIDS ን የመከላከል ትምህርት
- በ HIV ለተያዙ የሚሰጥ የመከላከል ጣልቃ ገብነት እና የጤና ትምህርት
- በባህል እና በቋንቋ የሚቆራኙ የትምህርት ቁሳቁሶች
- የሕክምና ጉዳይ አያያዝ
- የህክምና ተሚጋችነት
- የአእምሮ ጤና ማማከር
- ለቤቶች ፣ ለቅጥር ፣ ለህዝብ ድጋፍ ፣ ለምግብ መደርደሪያ ፣ ለልብስ ፣ ለትምህርት ፣ ለህጋዊ ፣ ለቤት ቁሳቁሶች እና ለሌሎችም ፍላጎቶች የሚሆኑ ግብአቶች እና ሪፈራል ፡፡

### ነፃ የ HIV ምርመራ ጣቢያዎች

SAYFSM ---------------------------- 651-644-3983

JustUS Health ---------------------- 612-341-2060

Red Door---------------------------- 612-543-5555

### ይመርመሩ!

ሁሉም የምርመራ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በ SAYFSM ጽ/ቤት በነፃ የሚሰጡ ናቸው፡፡

SAYFSM የደም ምርመራን የሚያከናውነው በደንብ በሰለጡኑ እና የምስክርነት ወረቀት ባላቸው ሰራተኞች የሚከናወነውን መደበኛ ፈጣን የ HIV ምርመራ ኪት / ኦራኪዊክ ኪት በመጠቀም ይሆናል ፡፡



ቀጠሮ ለመያዝ ለ SAYFSM ይደውሉ እና የሠራተኛ አባላትን ጋር ይነጋገሩ።

የምርመራ ውጤቶች በ 15 ደቂቃዎች ውስጥ፡፡

**አድራሻችን:**
SAYFSM
2395 University Avenue, #200,
St. Paul, MN 55114

ስልክ ቁጥራችን: (651) 644-3983
ኢሜይል: info@sayfsm.org
ድረ ገፅ: www.sayfsm.org

### ልገሳዎች በደስታ ይስተናገዳሉ!

አዎ! ለ SAYFSM ማበርከት እፈልጋለሁ:
____$25 ____$10 ___$5 ____ሌላ

እባክዎ ልገሳዎን ለ:

SAYFSM
2395 University Avenue W, #200
St. Paul, MN 55114

**አናመሰግናለን!!**

ባህላዊ ተስማሚ የሆኑ አገልግሎቶችን ማቅረብ


በሚኔሶታ ውስጥ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ወጣቶች እና የቤተሰብ አገልግሎቶች (SAYFSM) ሚኔሶታ ውስጥ ላሉት አፍሪካውያን ሁሉ በባህላዊ ስሜት እና በቋንቋ ተስማሚ የ HIV/AIDS ትምህርት እና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ይሰጣል ፡፡

# Mbiu

የ SAYFSM መፅሔት 19/ፌብሩዋሪ 2022 የታተመ St. Paul, MN

651-644-3983 www.sayfsm.org info@sayfsm.org

## HIV/AIDS ን መዋጋት



ኤልደር ዳንኤል ባሰዌቲ

የዩናይትድ ሴንትራል ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በሚኔሶታ ውስጥ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ወጣቶች እና የቤተሰብ አገልግሎቶች ጋር በመተባበር አባላቱን እና የብሩክሊን ፓርክ ማህበረሰቡን የHIV/AIDS ን ወረርሽኝ መከላከል አስመልክቶ በማስተማር ረገድ በንቃት በመሳተፍ ላይ ይገኛል።

እንደ ቤተ ክርስቲያን በወር አራት ጊዜ ለአባሎቻችን መረጃ እናቀርባለን። መረጃው ባህልን የጠበቀ እና ተገቢና ለመረዳት ቀላል በሆነ ቋንቋ የቀረበ ነው። በዚህም፣ በእድሜ፣ በፆታ እና በተጋላጭነት ላይ በመመስረት የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማግኘት እንችላለን። HIV እንዴት እንደሚተላለፍ እና ኮንዶም በመጠቀም እንዴት መከላከል እንደሚቻል አስመልክቶ በየወሩ ወደ 250 የሚሆኑ ሰዎችን በትምህርት እንደርሳለን። እንደ ቤተ ክርስቲያን ግን፣ አደገኛ ባህሪያትን ማስወገድ እና እስከ ጋብቻ ድረስ መታቀብ እና ለአንድ አጋር ታማኝ መሆን ይህንን ወረርሽኝ ለመዋጋት እንደ አስተማማኝ መንገድ አጽንዖት እንሰጣለን።

አባላቱንም ከHIV/AIDS ጋር በተያያዙ መገለሎች እና ሁኔታቸዉን እንዲያውቁ በበጎ ፈቃደኝነት በሚደረጉ ምርመራዎችን አስመልክቶ አስተምረናል። ትኩረት ያደረግንባቸውም እናቶች፣ አባቶች እና ልጆች ናቸው። ከርዕሰ-ጉዳዩ ባህላዊ ስሜት የተነሳ ስለ HIV/AIDS በነፃነት መወያየት ፈታኝ ሆኖ ቆይቷል። ሆኖም፣ መሻሻል አለ፣ እና ለ SAYFSM ትብብር እናመሰግናለን።

> “. . . HIV ለሌሎች ሰላምታ በመስጠት፣ በመተቃቀፍ እና በጋራ በመመገብ አይተላለፍም።”

በተከታታይ ትምህርታችን ምክንያት ብዙ አድማጮቻችን በተለይም በጾታ ግንኙነት ላይ ያሉ ወጣቶች እና ያላገቡ ለትምህርቱ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተው ለምርመራ ሄደው የHIV/AIDS ሁኔታቸውን አውቀዋል። HIV ለሌሎች ሰላምታ በመስጠት፣ በመተቃቀፍ እና በጋራ በመመገብ እንደማይተላለፍ ለአባላቱ አስተምረናል። ይህም በHIV ከተያዙ ሰዎች ጋር በሚገናኙበት ጊዜ በሰዎች ላይ ያለውን ስጋት አስወግዷል። እነርሱም እንደቀደሙት ጊዜያት ማግለል ትተው እንዲያውም በቤተክርስቲያን አገልግሎቶች እና እንደ ሰርግ ፣ የልደት በዓላት እና በዓላት ባሉ ሌሎች ማህበራዊ ስብሰባዎች ላይ በነፃነት ከእነሱ ጋር መቀመጥ ጀምረዋል። ይህ HIV/AIDS ን በመዋጋት ረገድ ትልቅ እርምጃ ነው። በቫይረሱ የተያዙ አባላት ለወንድሞቻቸው እና ለእህቶቻቸው የበለጠ ክፍት ሆነው በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅነት እና አቀባበል ሲደረግላቸው ለማየት ችለናል ምክንያቱም በህብረተሰቡ ዘንድ የሚጠሉ አይደሉም። ልጆቹ አብረው መጫወት እና ብዙ ጓደኞች ማፍራት ይችላሉ።

ወረርሽኙ አሁንም እንደቀጠለ ነው፣ እናም ትኩረታችንን ማጣት የለብንም ይልቁንም ተጨማሪ ግብአቶችን ማፈላለግ እና ይህንን ወረርሽኝ በ 2030 ለማቆም ከፈለግን ጥረታችንን በእጥፍ ማሳደግ አለብን።

*ኤልደር ዳንኤል ባሰዌቲ፣ የዩናይትድ ሴንተራል SDA ቤተ ክርስቲያን*


## HIV ን እንዋጋ - ከ HIV ጋር የሚኖሩትን ሳይሆን

ሰዎች በ HIV የተያዙ እንደሆነ ማወቅ አይፈልጉም ፣ ምክንያቱም ቤተሰቦቻቸው እና ማህበረሰባቸው እንዳይፈርድባቸው እና እንዳያገሉዋቸው ስለሚፈሩ ነው ፡፡ HIV/AIDS ያለባቸው ቢሆንም እንኳ ሁሉም ሰው ሁልጊዜም እንደሚወደድ እና እንደሚደገፍ ማወቅ አለበት ፡፡

AIDS ን የሚያስከትለው ቫይረስ በንክኪ ፣ በምራቅ ፣ በእንባ ፣ በማስነጠስ ፣ በሳል ወይም በማንኛውም ዓይነት ተራ የሆነ ንክኪ አይሰራጭም ፡፡ HIV በዋነኝነት የሚተላለፈው HIV ቫይረስ ካለበት ሰው የዘር ፈሳሽ ፣ የሴት ብልት ፈሳሽ ፣ የፊንጢጣ ፈሳሽ ፣ ደም ወይም የጡት ወተት ነው ፡፡







ከ SAYFSM የውጭ ተደራሽነት ጉዳዮች አስተባባሪ
ፍቅሩ ኢቲቻ

## ሁላችንም በዚህ ውስጥ አብረን ነን

ለቅርብ ጊዜ መሻሻሎች ምስጋና ይግባውና የ HIV ምርመራ አሁን ፈጣን እና ቀላል ነው ፡፡ ለ HIV ምርመራ ለማድረግ ድፍረቱ የሚመነጨው ለጤንነትዎ ሃላፊነት ከመውሰድ እና ለማህበረሰብዎ ከማሰብ ነው ፡፡ በተለይም ቀደም ብለን በምንመረመርበት ጊዜ ፖዘቲቭ የምርመራ ዉጤት ያገኙትን ለማከም እና ለመንከባከብ የቀለለ መሆኑን መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡

ምርመራ ያደረጉ ሁሉ ከምርመራው በፊት እና በኋላ የምክር አገልግሎት ያገኛሉ ፡፡ አጭር ምክር እና ፈጣን ምርመራ የ HIV ሁኔታዎን ለማወቅ እድል ይሰጥዎታል እናም በህይወትዎ ውስጥ አዎንታዊ ለውጦችን እንዲያደርጉ ይረዳዎታል ፡፡

**የምርመራ ውጤትዎ ነገቲቭ ከሆነ** የ HIV ምርመራ እና የምክር አገልግሎቱ ከቫይረሱ ተላቀው መቀጠል እንዲችሉ ኃይል ይሰጡዎታል ፡፡ እንዴት ነገቲቭ ሆኖ መቀጠል እንደሚችሉ ግልፅ እና ተጨባጭ እቅድን ይዘው ከምርመራ እና ከምክር ክፍለ ጊዜው የሚወጡ ይሆናል።

**የምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ** አማካሪው ረጅም እና ጤናማ ሕይወት ለመኖር የሚያስችልዎትን የሕክምና እንክብካቤ እና ድጋፍ እንዲያገኙ ይረዳዎታል ፡፡ SAYFSM HIV ፖዘቲቭ ለሆኑ አፍሪካውያን ብዙ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሲሆን አዲሱን ተግዳሮትዎን በተሳካ ሁኔታ ለማሸነፍ የሚያስፈልግዎትን ድጋፍ ይሰጥዎታል ፡፡

ሁላችንም በዚህ ውስጥ አብረን ነን፣ እናም ይህንን ጉዳይ በሐቀኝነት ለኅብረተሰባችን ማሳወቅ መቻላችን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የመጀመሪያውን እርምጃ ይውሰዱ፡ የ HIV ምርመራ ያድርጉ ፡፡ ከዚያ ጓደኞችዎ እና ቤተሰቦችዎ እንዲሁ እንዲያደርጉ ያበረታቱ።

## ስለ HIV መወቅ ያለብዎት ነገር ምንድን ነው?

“እውቀት ከሀብት ይሻላል።”
የካሜሩንያን አባባል

HIV/AIDS ምንድን ነው?

- **HIV AIDS ን የሚያስከትል ቫይረስ ነው ፡፡ ሰውነታችንንም ከበሽታዎች እና ኢንፌክሽኖች የሚከላከለው የሰውነት ተፈጥሯዊ የመከላከያ ዘዴ የሆነውን በሽታ የመከላከል ስርዓትን ይጎዳል ፡፡**
- **በበሽታው ከተያዙ በኋላ፣ የበሽታ ምልክት ሳይኖርብዎት ወይም በ HIV መያዝዎን ባለማወቅ ለብዙ ዓመታት መኖር እና ለሌሎች ማስተላለፍ ይችላሉ ፡፡**
- **ለዓመታት በ HIV ከተያዙ በኋላ በሽታ የመከላከል ስርዓትዎ በጣም ይጎዳል እናም ኢንፌክሽኑም ወደ AIDS ያድጋል ፡፡**
- **AIDS ማለት የ HIV የመጨረሻ ደረጃ ነው ፡፡**
- **AIDS ን ለይቶ ማወቅ የሚችለው ዶክተር ብቻ ነው ፡፡**
- **ለ HIV/AIDS ምንም አይነት ክትባት ወይም መድኃኒት የለም ፡፡**
- **ምንም እንኳ የደህንነት እርምጃዎች ስራ ላይ ካልዋሉ ወይም መርፌ ያጋሩ እንደሆነ አሁንም HIV ን ወደ ሌሎች ሊያስተላልፉ ቢችሉም፤ በ HIV የተያዙ ብዙ ሰዎች ጤናማ እና ረጅም ህይወት እንዲኖሩ ለመርዳት ህክምና ይሰጣል ፡፡**
- **ከህክምናዎቹ ተጠቃሚ ለመሆን ቀደም ብለው የ HIV ውጤትዎን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡ የ HIV ውጤትዎን ማወቅ የሚችሉት የ HIV ምርመራ በማድረግ ብቻ ነው፡፡**

**HIV አይለይም!**
**ማንኛውም ሰው በ HIV ሊያዝ ይችላል!**